ጋለሪያ ቶሞካ GALLERIA TOMOCA

ቸርነት ወልደ ገብርኤል ያቀርባል PRESENTS **Cherinet Welde gebriel**



# “የሥዕላዊ እና ቃላዊ ጥበባት ቡረቃ ”

## የግጥም እና ሥዕል ትርዒት

ሰኔ ፳፮ ፳፻፯ ዓ.ም.

# Artistic Jubiliation

## Painting & Poetry Exhibition

July 03/2015

(የፊት ሽፋን)

አብሮነት

(On the cover) /

Togetherness

April 03/2015
Presented by Galleria TOMOCA
Art Director - Eshetu Tiruneh
Managing Director - Nebiyu Girma
Editor - Nafkot Yoseph
Printed by Central Printing Press

**ይዘት**

የሥዕላዊና የቃላት ጥበባት ቡረቃ ፫

“እውነትም ፣ ውበትም ፣ አሁን ነው ልካቸው!” ፰

## Contents

Artistic Jubiliation 3

Cherinet and his pursuit for marriage of the arts 8

# ጤና ይስጥልን!

**እንኳን ወደ ጋለሪያ ቶሞካ አስራ ስድስተኛው መንቶ የጥበብ ትርዒት በደህና መጣችሁ! አንድ ፣ ሁለት እያለ ብዙ የጥበብ አድናቂዎችን እየሳበ የመጣው ጋለሪያ ቶሞካ በአሥራ ስድስተኛው ዙር የጥበብ በረከት ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤልን ይዞላችሁ ቀርቧል። የሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤል የዕይታዊና የቃላዊ ጥበባት ፣ የሚታዩና የሚነበቡ መንቶ ትርዒት ናቸው ። ቀደም ሲል በቶሞካ ቤተ ሥዕል ማሳያ ከታዩት ፣ በዓይነቱ የተለየና የመጀመሪያው ነው ። ሥነ ሥዕልና ሥነ ግጥም መሳ ለመሳ የሚቀርቡበትን ይህን ትርዒት ከሰርክ አዲሱ ፣ በተለየ ቃና ፣ ጣዕምና መዓዛ ከምትወዱት ፣ ከትኩሱ የቶሞካ ቡና ጋር እንድትዝናኑባቸው እነሆ ብለናል።**

**መልካም ዕይታ!**

# Welcome

Featuring the various talents of Ethiopian artists has been an exciting experience for Galleria Tomoca. And now we are on the sixteenth turn of this feat. This month Galleria Tomoca is bringing you a special collection of visual and poetic art with Chernet Wolde Gebriel. This is the first time that such a combination is featured at our Gallery, and probably the first in Addis Ababa. Take pleasure of the rainy season with your uniquely favourite coffee ,Tomoca, and with the passionate dual artist’s pieces.

Enjoy your visit!

## የሥዕላዊና የቃላዊ ጥበባት ቡረቃ

በቶሞካ ቤተ ሥዕል ማሳያ /ጋላሪያ ቶሞካ / የቀረቡት ፤ የሠዓሊ ቸርነት ወልደ ገብርኤል የዕይታዊና የቃላዊ ጥበባት ፤ የሚታዩና የሚነበቡ መንቶ ትርዒት ናቸው ። ቀደም ሲል በቶሞካ ቤተ ሥዕል ማሳያ ከታዩት ፤ በዓይነቱ የተለየና የመጀመሪያው ነው ። ምናልባትም በአዲስ አበባ ጭምር ቀዳሚው ትርዒት ሳይሆን አይቀርም ። ሳይሳካ ቀረ እንጂ፤ ይህን ዓይነቱን መንቶ ትርዒት በሠዓሊ አገኘሁ አዳነ የሥዕል ትርዒት ላይ ተመኝተነው ነበር ። በእርግጥ መንቶ ትርዒት ሥነ ግጥም ከሥነ ሙዚቃ ጋር ፤ በተለያዩ ምሽቶች በተከታታይ ለአድማጮችና ለተመልካቾች መቅረብ ከጀመረ ዓመታትን አስቆጥሯል ። በታዳሚው ሕዝብም ተቀባይነትንና አድናቆትንም አግኝቷል ። አሁን ደግሞ ፤ ሥነ ሥዕል ከሥነ ግጥም ጋር ይኸው አንድ ብሎ ጀምሯል ። እኛም ፡ ወደፊት እንዲህ ዓይነት ሠዓልያን ከመጡ ፤ እናበረታታለን ። ነባራዊው ሁኔታ ፈቅዶ አመቺ ጊዜና ቦታ ሲገኝ ፤ ሁሉም ጥበባት መሳ ለመሳ የሚቀርቡበት ትርዒትና መድረክ የማዘጋጀት ዕድል ይኖረናል። ለዛሬው ግን ፤ የሠዓሊ ቸርነት ወልደ ገብርኤልን መንቶ የጥበብ ትርዒት ጀባ ብለናል ።

የሠዓሊ ቸርነት ወልደ ገብርኤል መንቶ የሥዕልና የግጥም ጥበባት ፤ የእሱነቱ መገለጫዎች ናቸው ። እሱነቱ ለተፈጥሮ ፤ ለሕይወትና ለኑሮ ያለውን አመለካከት ተከፋፍለው ይገልጻሉ ። በሥዕል የሚታዩትን በሥዕል ፤ በቃል የሚነበቡትን በቃል ገልጿል ። የሥዕላዊ ኪነ ቅቦቹ በሕብረ ቀለማት በአብዛኛው የአካባቢውን የተፈጥሮ ገጽታዎችን የመልክዓ ምድርን ፤ የመልክዓ ሰብ ምስልን ፤ የመልክዓ አበባን ወዘተ ሲገልጹ ፤ የጽሑፋዊ ሥነ ግጥሞቹ በኅብረ ቃላት የሕይወትንና የኑሮን ፤ የፍቅርንና የጥላቻን ምንነትና ጥያቄዎች ያነሳሉ ያወርዳሉ ፤ በጉልህም ያንጸባርቃሉ ። ሁለቱም ጥበባት ሕብረ ቀለማትና ኅብረ ቃላት ለአገላለጻቸው ኃይልና ጉልበት አላቸው ። ሰላምና ጸጥታም ።

ሠዓሊ ቸርነት ወልደ ገብርኤል በተለይ በኪነ ቅቦቹ የሚዳስሳቸው ርእሰ ጉዳዮች ፤ በከፊል እውነታና በኢ እውነታ

## Artistic Jubiliation

Galleria Tomoca is bringing you a special work of arts and poetry with Cherinet Weldegebriel. The art collections appeal for both poem lovers and art admirers Cherinet is both a painter and poet. This is the first time that such a combination is featured at this gallery and probably the first in Addis Ababa. Of course there are shows that feature music and poetry but it is not common to see art exhibitions featuring poetry in the mix. We actually tried to link the two art forms in our previous exhibition by Agegnenhu Adane but that has not happened for various reasons. Now we are very happy to present you Cherinet's dual artistic pieces. We also encourage other artists with such dual talents to join us at Galleria Tomoca in the future. So that we will be having smooth opportunity to show case other forms of art combined and harmonized.

Cherinet expresses himself through his painting as well as poetry. Words and paintings are dual ways of expressing himself as medium of communication to the outside world. His paintings mostly show harmonious features of nature, landscape and portraits of people. In his poetry Cherinet demands answers for everyday life challenges, love, hate and wide range of social issues. Both of his expressions are powerful and strong in their own ways and seek understanding and peace.

His paintings are expressed in semi realistic and

/ semi realistic and semi abstract / ኪነ ሥዕላት የተገለጹ ናቸው ። የሥዕላዊ ሕብረ ቀለማቱ አደበላለቅና አገባብ ፤ የወፍራም ቀለም አወሳሰዱና የብሩሽ አመታቱ፤የቀለመ ቢላዋ (Palatte knife) አለጣጠፉ /impasto / ቀለማዊ ሻካልሴ / textures of colour /ፈጥረዋል ። ለምሳሌ :- በከፊል እውነታ የተቀቡት እቅፍ የጽጌሬዳ አበባዎች ፤ እንደገናም የጽጌሬዳ አበባዎች ከሴት ልጆች መልከዓ ምስላት ጋር ፤ የጫካውና የወንዙ ዳር ዳር ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ፤ ቅጠሎች ጭምር ወዘተ እንዳሉ በልጥፍ / impasto / ኪነ ቅብ የተቀቡ ናቸው ። የሕብረ ቀለማቱ አየራና የብሩሽ አመታት እንዲሁም የቀለመ ቢለዋ አለጣጠፍ ፍጥነቱና እንቅስቃሴው በሸራው ላይ በግልጽ ይታያሉ ። አንዱ ሕብር በሌላው ሕብር ላይ እጅግ የተደራረቡና የሰረጉ ናቸው ። በመሆኑም የሠዓሊውን ውስጣዊ ኃይልና ጉልበት ሲበዛ ያሳያሉ ። በእርግጥ ወደፊት ሠዓሊው ልብ ሊላቸው የሚገቡና የሚያጠያይቁ የሕብረ ቀለማት ኑባሬያት መፋለስ /discordant of colour harmonies/ እንዳሉበት ሳንረሳ ነው ።

እንደዚሁም ፤ የሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤልን ሥነ ግጥም ስናየው ፤ የሰው ልጅን የሕይወትንና የኑሮን ምንነትን ፤ የውስጣዊ ስሜትንና እሳቤን ፤ የፍቅርን የጥላቻን ጥያቄዎች ያነሳሉ ። ለመጥቀስም ያህል ፤- በማለዳው የወጣትነት ዕድሜዎቹ ዓመታት የጻፋቸውና ኤፍራጥስ ; በሚል በ1998 ዓም ካሳተመው አንድ የሥነ ግጥም መጽሐፉ ውስጥ ብንጠቅስ ታድሎ ; ፤ አራተኛ ; ፤ ነፍስህን ቀድሳት ; ፤ ጨረቃ ; ፤ ማነው ? ; ፤ እውነቱ ; ወዘተ የሚያሠርጹት የተለያየ ነገረ ሐሳብ አሳቸው ። ለምሳሌ :-

ልሥራ ብትይ ባርያ ቁጭ ብትይ ሥራ ፈት ፤
ያሉትን ይበሉ ባርነቱ ያዋጣል ግድ የለም ገፊበት ፤
የሰው አገር የሰው ነው ቢል እንኳን ተረቱ ፤

የሰው የራስ ይሆናል ይኸው ነው እውነቱ ፤ ;

ኤፍራጥስ ; 1992 ዓም ፤ ገጽ 100 ፤

የሚለው ሥነ ግጥማዊ ስንኝ ሻካልሴው ለኅሊና የሚቆረቁር መራር እውነታ ነው ። ይሻክራልም ይለሰልሳልም ፡ ፡ ለምን ?ቢሉ ፤መሻከሩ የሰው አገር የሰው ነው መቼም

semi abstract arts. The way he takes pigment of paints in and impasto. So the pigments create their own textures. His mixtures of colors and knife palate are clearly observed in his paintings. The way hi mix up the pigments of colors are also vivid in his works. You can look the roses, the roses and women and the forest and trees by the rivers to understand these expressions. You can even look at the intensity and swiftness of his strokes in the paintings. They show you the passion and power he exerts in his paintings. Of course there are some discordant color harmonies that Cherinet has to check in the future.

As stated above, the poems deal with life matters like love and hate, meaning of life and similar themes. His poetry collection published in 2004 titled "Efrates" has a number of wonderful pieces. Among these are "Tadilo(the lucky one)", Arategna (the fourth one), Chereka (The Moon) and Ewnetu (The Truth). Few lines from his piece titled "Efrates" with close literal translation from Amharic to English goes like this….

…..People call you lazy when you don't work

They call you servant and low life when you do

Let them say what they want

Just go on and be the underdog

Life may take you to another land being the underdog

But in time that another land will be yours….



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015

የራስ አይሆንም ::ባርነቱም እንደዚያው ነጻነትን ይገፋል : : መለስለሱ ደግሞ ሥራ የትም አገር ክቡር ነው :: በሰው አገር ሠርተው በልጽገውና ከብረው ዓይተናልና እሙን ነው :: ነገር ግን ሥራን ፤ ባርነትን ፤ የሰው አገርን አገርንና ነጻነትን በአንድ ሚዛን ላይ አስቀምጦ ሲመዝኑት የመራር እውነታው ሥራ ፤ ባርነት ፤ የሰው አገር ያረፈበት ጎን ሚዛኑ ይደፋል :: ነገር ግን ያው ተመልሶ አገር አገር ነው ፤ ነጻነትም እንዲሁ ::

ደጋግመን ማንሳትና ማገናዘብ ያለብን ፤ማንኛውም የፈጠራ ጥበብ መነሻው ተፈጥሮና ኅብረተሰቡ ሲሆን ፤ መዳረሻው ግን ፤ ዓይቶና አንብቦ የሚረዳው በቀዳሚነት በዚያው ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው የጥበብ አፍቃሪና አድናቂ ነው:: በለጣቂነትም መሳው የሰው ልጅ ይሆናል :: ለፈጠራ ጥበብ ውጤት የሰው ልጅ ጥልቅ ስሜትና የሚያስብ አእምሮ ዓይነተኛ መናኸሪያው ነው :: ዓይነ ልቦናውንና እዝነ ልቦናውን አስቀድሞ ሳዘጋጀ ተመልካችና ሰሚ ደግሞ ጥበባዊ እርካታው የበዛ ነው :: ጥበባዊ ፍቅሩ ሳለውማ ጣዕመ ስሜቱና እርካታው የትዬለሴ ነው :: የሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤልን ሥነ ቅብንና ሥነ ግጥምን የሚያዩና የሚያነቡ ታዳሚዎች የተለየ መንታ እርካታ እንደሚያገኙበት አያጠራጥርም ::

ሥነ ቅብንና ሥነ ግጥምን ሳቀረበልን ለሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤል ያለኝን አድናቆትና አክብሮት እየገለጽኩ ፤ ቶሞካም ከዘወትር ጣዕመ ቡናውና ስሉጥ መስተንግዶው ጋር የተለመደ የጥበብ ደጋፊነቱን እንዲቀጥል ፤ ተመልካቹም ጣዕመ ቡናውን እያጣጣመና በኪነ ሥዕላቱ እየተዝናና እንዲደሰት ፤ መልካሙን ኹሉ እየተመኘሁ ፤ እስከ የሚቀጥለው የሥዕል ትርዒት በዚሁ እሰናበታለሁ :: በሰላም ያገናኘን ::

እሸቱ ጥሩነህ
/ሠዓሊ/
ግንቦት ፳፻፯

## ፈጋ በረዎች

ፈጋ በረዎች በአንድነት

አስደንብሯቸው የወፍ ፉጩት

በማሳው ላይ ሳለ ሰብሉ

ሳይታጨድ ወቁት አሉ::

ሚያዝያ 10/1993

In this piece Cherinet tries to show us the hard truth about living in another land. But at the same time shares the important place of hard work wherever you are to keep you out of misery.

Art always looks for a place in the minds and hearts of human beings. When that natural place is ready, we have some very talented people like Cherinet who bless us with their artistic gifts. Thanking Cherinet for presenting us with his dual artistic gifts, I leave you to enjoy the pieces.

As usual I want to appreciate Galleria Tomoca for arranging such a platform to enjoy art, sipping the amazing taste of Tomoka Coffee. Thank you and See you soon with another feature.

Eshetu Tiruneh (Painter)
May 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



## ‹‹እውነትም ፤ ውበትም ፤ አሁን ነው ልካቸው!››

ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤል

አንዲት ኢትዮጵያዊት ሐኪም እና አንዲት በልመና ሳይ የተሰማሩ ባልቴት ነበሩ፡፡ ከአሥርት ዓመታት ቀድሞ የነበረ ታሪክ ነው፡፡ በባልቴቷ እና በሃኪሟ መካከል የእናት እና የልጅ ግንኙነት አለ፡፡ እናት ልመናውን ይወዱታል፤ያከብሩልም፡፡ልጅት ደግሞ ይህንን እውነት ለመቀበል ተቸግራለች፡፡ ሥር የሰደደ አለመግባባትም በመካከላቸው ፀንቷል፡፡ የሁለቱም እውነት ለየራሳቸው ልክ ነበር፡፡ ባልቴቷ ልመናውን ከመጠበብ ጋር ያያይዙታል፡፡ ለልጅ ደግሞ ይህንን መሰሉ ጥበብ የሚዋጥ አልነበረም፡፡ ልብ በሉ! ተረት ሳይሆን እውነት ነው፡፡

ራጉኤል ቤተክርስትያን ደጃፍ ሳይ የእኒህን ባልቴት የልመና ጥበብ እንደዋዛ ማለፍ ከባድ ነበር፡፡ በውብ ቋንቋ፤ ሥነ ግጥማዊ በሆነ ስልት፤ በዝማሬ ለርሳቸው ልመና ያልሆነውን ልመና በቃላቸው ሲያንቆረቁሩት ብዙዎች ይመሰጣሉ፡፡ ባልቴቷን ሳይመፀውቱ ማለፍ ይከብዳል፡፡ ልጆቻቸው ትርጉም ያለው ዕውቀትና ሙያ፤ ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ ባለቤትም ናቸው፡፡ የገንዘብ ችግር የለባቸውም፡፡ እናት ግን ይለምናሉ፤ ምፅዋትም ይቀበላሉ፡፡ ለልጆቻቸው እና ለመፅዋቾቹ ይሄ ምፅዋት ከምፅዋት የተለየ ትርጉም የለውም፡፡ለባልቴቷ ግን ምፅዋት አልነበረም፡፡ለርሳቸው ሽልማት ነው፡፡ የጉዳዩ ሽልማትነትና ምፅዋትነት ቤተሰቡን ሲያወዛግብ ቆይቷል፡፡

የሚገርመው ነገር ይህንን ምጽዋት መልሰው በድብቅ ለሌሎች

## Cherinet and his pursuit for marriage of the arts

There was once a controversial old woman living in Addis. Despite having decent life, she was one of the regular beggars attracting most worshippers at the gate of one of the popular churches in the center of Mercato, St-Raguel. She was liked by many for her extraordinarily artistic approach and style of begging. She was not like the many ordinary beggars that we know. She was attracting the attention of many for her brilliant poetic talent, beautiful language and the melodious approach that she was accustomed to while practicing begging. She never thought of her practice as begging. Rather , she took herself as passionate entertainer making to relax. Surprisingly, it was lately known that the lady was giving the coins to the needy in her surroundongs.

One of her daughters, who is a physician by profession, had always been emotionally torched by her mother's acts. The whole family was highly challenged to neither take it positively nor to force her quit her practice. Life went on like that. Nothing was able to change her mind.

ችግረኞች መመጽወታቸውን ነው።

እኒህ ባልቴት የቄስ ወልደ ገብርኤል ሲሳይ አክስት ናቸው። ቄስ ወልደ ገብረኤል በራጉኤል ቤተክርስትያን አገልጋይ ነበሩ። የቅኔ ዕውቀታቸው ከፍ ያለ እንደነበር ቸርነት ይናገራል።

ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደ ገብርኤል በዚህ የዘር ሠንሰለት ወይም ግንድ ዝቅ ብሎ የሚገኝ አንጓ ነው። በአባቱ መንገድ ከራጉኤል ቤተክርስትያን ድቁናን ተቀብሏል። ቤተክርስትያኒቱን በድቁና ወደ ማገልገል ግን አልሄደም። የኣባቱ አክስት (ባልቴቷ) እና አባቱ፤ ቄስ ወልደ ገብርኤል ሲሳይ፤በቸርነት ጥበባዊ ስብዕና በተለይም በገጣሚነቱ ላይ ደማቅ አሻራቸውን አሳርፈዋል። ከንባብና ከፅሑፍ ጋር ስተያያዘ ማንነቱ የነዚህ ሰዎች ተፅዕኖ የጎላ ነበር።

ቸርነት ወልደ ገብርኤል የጣምራ ጥበብ ባለቤት ነው። ሠዓሊነትና ገጣሚነት ለቸርነት መንታ ቅፅሎቹ ናቸው። ለገጣሚነቱ ያነሳነው ተፅዕኖ እንደተጠበቀ፤ ለሠዓሊነቱም ባለድርሻዎች አሉ። በመድኃኒዓለም ት/ቤት የንድፍ (drawing ) መምህር የነበሩትና፤ ቸርነት ‹ቲቸርተስፋዬ› የሚላቸው አንዱ ናቸው። የቸርነት ታላቅና ታናሽ ወንድሞቹም በሥዕል ጥበብ ውስጥ አሉ። ታላቅ ወንድሙ በ‹ቲቸር ተስፋዬ› ሥዕልን አጥንቷል። ቸርነትም የታላቅ ወንድሙን ፈለግ ተከትሎ በ ‹ቲቸር ተስፋዬ› ንድፍን (drawing) እና ሥነ-ቅብን(painting) ለአራት ዓመታት ተምሯል።

የቸርነትን ሥነ ጥበባዊ ምንነት ከልጅነቱ መነጠል አይቻልም። በጎልማሣነት ዕድሜ ላይ ያለው ቸርነት መሠረቱ የተጣለው ያኔ ነው። በልጅነት የወንድሙን ሥዕላዊ ሥራዎች እንዳሉ ለመቅዳት፤ በት/ቤት በክፍል ውስጥ የመምህራኑን ቁመና፤ አኳኋንና እንቅስቃሴ እያስተዋለ ለመንደፍ ይጥር ነበር። የጥበብ ፍላጎቱና ተመስጦው እንዲያ ተጠነሰሰ። በዚህ መንገድም ከመክሊቱ ተገናኘ። በልጅነት የተረዳውን ተሰጥዖ ለማበልፀግም የተለያዩ ጥረቶችን አደረገ። ለዘጠኝ ያህል ዓመታት የዕይታ ጥበብ ስልጠናውን ተከታትሏል።

በ1993 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አለ ፈለገሰላም የሥነ ጥበብና ዲዛይን ት/ቤት ከመግባቱ አስቀድሞ ለአምስት

She was an aunt to Wolde-Gebriel Sisay, a Priest in the same church; a distant aunt to Chernet Woldegebriel, a painter and poet, who was the only one being influenced by her creative artistic talent.

Poetry is also something that Cherinet's distant aunt was very good at. Cherinet has a special bond with her as he was inspired by how she uses poetry in her everyday life to communicate things that she wants to address.

Cherinet says;"My distant aunt from my father had a very interesting personality. Despite living a decent life, she accepted coins as a beggar in exchange for her poetry lines to people. She used to say that it is a prize and recognition of her talents and she was very good at it."

This has helped Cherinet to form a stronger connection with poetry and his talents were molded into a very good one over the years, both in writing poetry and painting. His younger brother also writes poems.

Most people in the world of art get their inspiration and career defining experiences as a child. Cherinet Weldegebriel had such an experience. He grew up admiring and getting captivated by the art works of his two brothers, who were already accomplished painters. That fascination grew into practice as he started copying paintings of his older brother. Cherinet also took his skills to the classroom and started drawing sketches of people and objects in the school including portraits of his teachers in a comical way.

Born on 28 January 1975 around Merkato area in Addis Ababa, in a family that treasures art in its different forms, Cherinet says his childhood is strongly influenced

ዓመታት የንድፍ (drawing) ስልጠና ወስዷል። በ1996 ዓ.ም ከአለ ፈለገሰላም የሥነ ጥበብና ዲዛይን ት/ቤት የመጀመሪያ ዲግሪውን ተቀበለ።

ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤል ጥር 20፤1967 ዓ.ም፤ መርካቶ ሰባተኛ አካባቢ ተወለደ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትሏል። ዛሬ የሙሉ ሰዓት ሠዓሊ ነው።

ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤል ባለ ትዳርና የሁለት ልጆች (የአንድ ወንድና የአንድ ሴት ልጅ) አባት ነው። ባለቤቱ ሩት ሰለሞን የፖለቲካል ሣይንስ ተመራማሪ ነች። በፖለቲካል ሣይንስና ዓለማቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪ፤ በሰብዓዊ መብት (Human Rights) የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁም በልማትና ድህነት ግንኙነት (Development & Poverty) በእንግሊዝ ብራይተን ከተማ ከሚገኘው ሱሴክስ ዩኒቨርስቲ ተጨማሪ የማስተርስ ዲግሪዋን ተቀብላለች።

ሩት ሰለሞን የሥዕል አፍቃሪ ናት፤ ባለቤቷ ቸርነት እንሚለው ስለ ሥዕል ብዙ አንብባለች። ይሄ ንባብ ወደ ሠዓሊነት ባይወስዳትም ስለ ሥዕል የበሰለ ሀሳብና ትችት የመስጠት አቅምን ግን አድሏታል። የቸርነትን ጨምሮ ስለተለያዩ ሥዕላዊ ስራዎች የጠለቀ አስተያየትንም ትሰጣለች። ቸርነት እንደሚለው የባለቤቱ የሩት ሁለገብነት በጥበባዊ ስብዕናው ላይ የደመቀ ማህተሙን አሳርፏል።

ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤል በ1998 ዓ.ም ‹ኤፍራጥስ› የተሰኘ የግጥም መድብል አሳትሟል። በ2002 ዓ.ም ከሙዚቃ ጋር የተቀናበረውና በሲዲ ታትሞ ለአድማጭ የቀረበው ‹ዲና› የተሰኘ የጥበብ ፍሬውም አይረሳም። ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤል በከተማችን እየተለመደ በመጣውና ግጥምና ጃዝ ሙዚቃን ባዋሃደው አዲስ ባህል ውስጥም የጎላ ተሳትፎ አለው። ‹‹እውነትም፤ ውበትም፤ አሁን ነው ልካቸው!›› የሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤል ፍልስፍና ይመስላል። ጋላሪያ ቶሞካ አንድም፤ ሁለትም ገፅ ያለውን፤ ሠዓሊና ገጣሚ ቸርነት ወልደገብርኤልን ይዞላችሁ ቀርቧል። ለቸርነት በግሉ ዘጠነኛው ሲሆን፤ ለጋለሪያ ቶሞካ ደግሞ አስራ ስድስተኛው የሥዕል ትርዒትነው።

ነብዩ ግርማ

by his father's Christian background. As a priest, his father would take him to church and Cherinet practices spiritual singing and also spent time studying the bible.

"Myartistic personality and profession was shaped during my wonderful childhood with the influence and support of a great family." says Cherinet.

Cherinet is a graduate of the School of Fine Arts and Design. After graduating in 2004, he taught drawing and painting in different schools including Addis Ketema Secondary School, Music Mayday and Ethio Turkish School.Cherinet showcased his art works in eight solo and five group exhibitions, one of which is in the Netherlands.He published one poetry book titled "Efrates" in 2005 and released a poetry CD in 2009 with a title "Dina". His second book is also in the making.

As a painter and poet, Cherinet enjoys the wonderful support of his wife who also shares his passion, although her day job is far from it. As she is well read in areas of painting and the art history, she critically reviews his works and at times tries to copy and paint some of his paintings. Cherinet's wife is a development practitioner with a bachelor's degree in human rights and post graduate qualification in development and poverty, earned at Sussex University in England, Brighton.

The couple has two children and most of the home responsibilities are handled by his wife. "I am blessed to have such a loving and very supportive wife. She takes care of the responsibilities I should handle in the house and also makes sure that I am in the best environment to do my art work," says Cherinet.

Nebiyu Girma

# ዛሬም እሰክርሻለሁ

ከቀን ሩጫ ከድካሜ ፣

ትንሽ ፋታ ሳገኝ እንዳቅሜ ፡፡

ትዝታሽ ነው አጫዋቼ - ሳይጠሩት አቤት አለሁ ባይ፣

ሞኝ አይደለሁ በሕግ አምላክ እልል - ባገሬ ሕግም አምላኩን አይዳኝ ፣

እኔም ተው አትምጣ አይወጣኝ፣

እሰይ፡፡

የጉርምስና ጉልበቴን - መቅኔዬን አቅልጬ፣

ቀን ከሌት ሳይደክመኝ - ሳልታክት ሮጬ፡፡

የመሰለኝ ድፍረት እውቀት፣

በእሳት እድሜ - በታጨቀ ትእቢት፣

እንኳን ልጅነቴ - እግርሽ ስር ዘራሁት፡፡

መቼም ጉርምስና - መድረሻው እንደማይታወቅ ንፋስ፣

የት ይነሳ - የት ይቁም - የት ይድረስ፣

እልም ነው - ሸው ነው፣

አልፎ እንደዚህ ካሳየነው፡፡

እኔማ ፡- ያን የልጅነት ሰመመን - እያመነዠኩ እጠግባለሁ፣

ጎረቤት በማይሰማው ሸለላ - ትዝታዬን እየጠጣሁ ዛሬም እሰክርሻለሁ፡፡

በዛ እሳት እድሜ -

እንኪ ልቤን ብዬ፣

ስንቅሽ ይሁን ብዬ፡፡

ከአዝማሪ አብሬ፣

ለፍቅርሽ ዘምሬ፣

በዛ እሳት እድሜ - አንቺ ብቻ ሆነሽ የኔ ቁም ነገሬ፡፡

እሰይ ቁም ነገር ጠላሁ - እንኳን በፌዝ አለፈ፣

የዛኔ ምሳሌ የነበር - አሁን ምን አተረፈ?

እንኳን ፈነዳሁ - ጧ አልኩ፣

ደግ አበጥኩ - ቀበጥኩ፣

እሹት ለቆንጆ አማርኩ - አጎፈርኩ፣

አበጀሁ ደረቴን ነፋሁ - በአካሄዴም እንኳን ነጠርኩ፣

እሰይ ቁም ነገር ጠላሁ - ደግ አደረኩ፡፡

ህፃን ሆኖ በውሃ - አድጎ ደሞ በእሳት፣

አይደለም እንዴ የሰው ስሪት ?

እኔማ፡- ያን የልጅነት ሰመመን - እያመነዠኩ እጠግባለሁ፣

ጎረቤት በማይሰማው ሸለላ - ትዝታዬን እየጠጣሁ ዛሬም እሰክርሻለሁ፡፡

ጥር 2007 ዓ.ም

## ጨረቃ

ሙሉ ሆነሽ፤

በጥቁር ላይ ነጥተሽ፤

በጭለማው ነግሰሽ፤

ፈክተሽ፤

ደምቀሽ ወጥተሽ፤

አየሁሽ፤

ታምሪያለሽ፡፡


አንቺ ሴት ብትሆኚ ወንድ ጨረቃም ቢፈጠር፤

ትበዙ ነበር በሰማይ ጨለማም አይኖር በምድር፡፡

ሚያዝያ 10/1993



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015

## መካሪ መች አጣው

መክሮኝ፣ ዘክሮኝ፣ መርቶኝ ነው የሄደ አውራዬ፣
ያ እንደመስቀል ደመራ ጭስ - ብን ሲል የታዬ::
ሁሉ እውነት ትክክል ነው ብዬ እንጂ - ሁሉ ትክክል እውነት ነው ብዬ፣
መች ተቀብዬ ::
ውበት ሳደንቅ - ለከት ባጣ - ባስጠላ ፣
ገል ቢያረገኝ ገላ::
በጣት ተፈራርሞ ፣
በስጋ ተኮራክሞ::
ልክ እንደ እኔው፣
የመጣ ሕያው፣
ተው ሲለኝ እሱ ሳይተው፣
መካሪ መች አጣው?

ጥር 2007 ዓ.ም

## ባለቤት ባለው አገር ስዞር

ጨለማው ሳይዘኝ እያደርኩ ደምቄ
አድባሯ ሳትጠላኝ ሳትገፋኝ ርቄ
በቀን በሚጨልም በማላውቀው ሀገር
ናፍቆት መዘለገኝ እንደምነው ሸገር?
እንደምነው ምሥራቅ እንደምነው ምዕራብ?
እንደምነው ሰሜን እንደምነው ደቡብ?
ሰፈሬስ መርካቶ ሰባተኛ እንዴት ዋለ?
ገጠሩስ እንዴት ነው ዝናብ ቀረ ጣለ?
ባሳቤ ሰፈሬ
በህልሜ ሀገሬ
ሳልሄድ መች አድሬ
የሰው አገር ሰው ጥርሱ ውሸት ወርሶ
ብልጭ ከማለቱ ድርግም ይላል ደርሶ
በሰው አገር ስዞር
ባለቤት ባለው አገር ስዞር
ሎ-ሎን አገኘሁት አፈር ላይ ተስሎ
ካፈር ተቀሳቅሎ
አገሬ ቢሆን ከፊደል ያልፋል ፍካሬ ትርጉሙ
እሮሮ ነው ፅንሱ ብሶት ነው ህመሙ::
እኔን የገረመኝ የኔው
ያልጮህኩት አብሬው!

2004

# ቀጠሮ ሰጥታኛለች

አየሩ እንደ ጥሩ ምግብ ጣፍጦ - ጨረቃም ያለወትሮዋ ተልቃ ፣
ከዋክብት ከሰው ሰራሽ ብርሃን ደምቀው - የጥሌም ነፍስ ከንፋሱ ሞዝቃ።
የገደል ማሚቱ የመሸበት እረኛ ግጥም አምጥታ- የቆሎ ተማሪን ቅኔ አካታ፣
የዛኔ፡- የሰማይ ባንዲራዊ ቀለም ቀስተ ደመና መቀነቷ - ከመሬት የተዝረከረከ ለታ።
ያቺ ጠይም እርግብ ኢትዮጵያዊ ብልጭልጭ ገሳዋን ይዛ - መጥታ ነበር፣
ደራሽ ወንዝ እንደንጉስ አጃቢ ዙሪያዋን ከቦ እየተንቀዠቀዠ - ጎብኝታኛለች ባአድ አገር።
አሁንም እጠብቃታለሁ፡-
ከእውቀት፣ ከማስተዋል፣ ከምልክት በቀር - ከወር፣ ከወቅት የራቀ፣
ቀጠሮ ሰጥታኛለች - ከቀን ከሰዓት የረቀቀ።
እናም ፡- አየሩ እንደ ኢትዮጵያ ከጣፈጠ- ጨረቃም ያለወትሮ ከተለቀ፣
የጥሌ ነፍስ ከንፋሱ ከሞዘቀ።
ምንድን ነው አልልም።
ኮከቦች ሲደምቁ - ግንድ የያዘው ብርሃን ሲበዥ፣
ወንዝ ወደ ላይ ሲፈስ- ሰኞ አርብ ላይ ሲንቀዠቀዥ።
ድንቢጥ የዶሮ ጫጩት ብትከጅል፣
ሣር አበባን ሲያሸት ቢውል፣
እንዴት ሆነ አልል።
ቀጠሮ ሰጥታኛለች ከቀን ከሰዓት የረቀቀ
ከወር ከወቅት የራቀ።

ግንቦት 2007



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015

## አየሩ አልተፈታም

ፍርሃት እንደ ጠመንጃ ተደቅኖ- ሰውም ባቋሙ ካልጸና፣
በነፃነት ስም ባርነት ነግሦ - በብርሃን ካልታየ ካቴና፣
ቀኑ ጨለማ ነው።
ሐቅ አስኝ ያስ - አይደስም ሲራመድ - ሲናገር ይጋጫል፣
የባለ ጊዜ ግዙፍ ስህተት እውነት ሆኖ - ባመኑበት መቆም ጅል ያሰኛል።
ቀን የሰራው ገደል- ለባለጊዜውም ገደል ነው - ዞሮ ሲያየው ሽንቱ ይመጣል፣
አየሩ አልተፈታም።
ይሄስ እንኳን የኔ አልሆነ - እሰይ የለሁበት በቀኑ፣
እሹት አብሬ ተራብኩ - ደግ ተጠማው ከብዙሃኑ።
እንጎሽ ዋልኩኝ ከጨረቃ - አበጀው አመሸው ካረቄ ቤት - ሴባን ሴባ ስል ከምታሰር፣
ምን በወጣኝ በማርያም ልጅ - ያስቀኔ የወጣች ፀሐይ - አይኔን ወግታኝ ምደናበር።

ሚያዝያ 2007


## እውነቱ

ልስራ ብትይ ባርያ ቀጭ ብትይ ሥራ ፈት፤
ያሉትን ይበሉ ባርነቱ ያዋጣል ግድየለም ግፌበት፤
የሰው አገር የሰው ነው ቢል እንኳን ተረቱ፤
የሰው የራስ ይሆናል ይሄ ነው እውነቱ።

2002



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015



Cherinet W/gebriel Dual Artist 2015

| የሠዓሊው ማህደር: - ቸርነት ወልደገብርኤል | Biography of the Painter- Cherenet Woldegebriel |
|---|---|
| ሥራ፡ ሠዓሊ / ገጣሚ | Occupation : Painter / Poet |
| የትውልድ ዘመን፡ መስከረም 28: 1975 ዓ.ም | Date of Birth : October 09: 1982 G.C. |
| የትውልድ ቦታ፡ አዲስ አበባ | Place of Birth : Addis Ababa |
| የትምህርት ደረጃ፡ ዲግሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አለ የሥነ ጥበብና ዲዛይን ት/ቤት | Education : Bachelor of Fine Arts & Design (BFA) Degree in Art Education and Painting from Addis Ababa University |

## Artist's Statement: Cherinet Welde gebriel Sisay

My interest and inclination to art goes back to my childhood. Copying drawings of my elder brother and sketching my teachers in class observing the different lines in their positioning and movement had always interested me when I was a child. Realizing my talent and interest of expressing my surroundings and ideas in conceptual dimensions of art such as lines, patterns and forms, after completing high school, I committed myself to developing my natural gift. I have attended visual art training for about nine years. I took training in drawing as amateur artist for five years before I joined Addis Ababa University (AAU), School of Fine Arts and Design, which is the only full-fledged professional Fine Art training institute in the country, in 2000 and studied Fine Art majoring in Painting for four years. Despite extremely competitive process where only twenty five out of more than one thousand applicants got admitted, I became one among those successful applicants. And that was one of the greatest achievements of my life and a landmark to my dream of pursuing a career as a professional artist. I graduated with Bachelor of Fine Arts & Design in 2004. Becoming a full time studio artist I have displayed my art work in a number of group and solo exhibitions held in Ethiopia and abroad.

As a painter my works focus on social and political phenomena and my aspiration of how things ought to be in life. I use colours from nature particularly landscape and flowers to express phenomena and ideal situations. I enjoy combining the diverse colours and different compositions in natural environs with my thoughts and expressing ideas and feelings distorting the forms. My enthusiasm to play with colours and different compositions has pushed me to stick to nature in my art work. Besides, I sometimes do portrait paintings though I focus on reflecting feelings rather than depicting outward looks. I use colours from landscapes and flowers to illustrate feelings and expressions. Beyond the diverse colours in flowers my belief that 'things happening today, at this moment, are always right and their moment of beauty and time is now. This thought of mine has somehow influenced my affection to flowers, flowers look beautiful more than anything at their blooming period and their time and beauty is that moment.

ጋለሪያ ቶሞካ

# ቸርነት ወልደ ገብርኤልን ያቀርባል

GALLERIA TOMOCA PRESENTS **Cherenet Welde gebriel**



ጋለሪያ ቶሞካ
አድራሻ ሳር ቤት
ከካናዳ ኤንባሲ ፊት ለፊት

**Galleria TOMOCA**
**Location: Sar Bet**
**In front of Canadian Embassy**
www.galleriatomoca.com